# <u>ፉኖ በል! ሞረሽ በል!</u>

## <u>ለአንተም ለእናት አገር</u>

ቀመሩ ደሳለኝ

ፉኖ ብለን እንነሳ በጀግንነት
ሞረሽ ብለን እንነሳ በድፍረት

አስተባብረን በቁርጥ ፅኑ አርበኝነት
ምንድነው ዝም ምንድነው ትግሥት
ምንድነው ችላው አለመቆጨት
ሕዝብ ሲባረር ሲዘረፍ ሃብት

ሰዎች ሲገፉ ሲቃጠል ቤት
በአገሩ መኖር ሲነፈግ መብት
ሲያጣ ነፃነት የዜግነት

ምንድነው ዝም ያለመናደድ ያለመቆጨት
ምንድነው ሽንፈት የልብ ፍርሃት
ወኔ መቀዝቀዝ ጀግንነት ማጣት?

ፉኖ ብለን እንነሳ በጀግንነት
ዘረኛ ወራሪን ድል ለመምታት
አገር፣ ወገን፣ ክብርን ላለማስደፈር ነፃነት
እንቁም በአንድ በኅብረት ለአንድነት
ኢትዮጵያ የሁላችን አገር በዜግነት
ሳይገድበን ቋንቋ ክልል በልዩነት
የወያኔ አምባገነን ጎጠኝነት
ኢትዮጵያ አንድ አገር ኅብረ-ብሔር በአንድነት
መኖር አለብን በእኩል ትክክል ለሁሉም መብት

ፉኖ ብለን እንነሳ  ለአገር ወገን አለኝታ
ሞረሽ ብለን ለማስከበር አገር ወገን በዜግነት አወንታ።
ለእናት አገር የሺህ አመታት ውድ ኢትዮጵያ
ለነበረው ላለውና ለትውልድ ሁሉ የሚሆን መኩሪያ
ፉኖ ብለን፣ ሞረሽ ብለን እንጠብቃት ለምንጊዜም መታፈሪያ።

የወያኔ  ቋንቋ ክልል አረመኔ ሥረዓት
የግፍ ጭቆና አምባገነን ሕግ- ወጥነት
በሕዝብ ላይ ክፉ በደል ትልቅ ውድቀት
ታሪክ አፍራሽ ሕዝብ አሳናሽ ከፋፋይነት
ጥላቻ- ክፋት አጎልብቶ መለያየት
አንድነት-ኅብረት ሲጠፋብን በአጉል ቅጥፈት
ምንድነው  ዝም ያለመቆጨት
ምንድነው ሽንፈት ወኔ-ቢስ ፍርሃት

ባገር ወዳድነት እንነሳ  ፋኖ ብለን በአንድነት
ባገር ኩራት እንቁ  ሞረሽ ብለን በድፍረት
ፋኖ ብለን እንታገል  ለእናት አገር ደህንነት
ሞረሽ ብለን በኅብረት  ለማይበገር ያገር እምነት
ፋኖ ብለን በተስፋ  ለግላችን ሃይማኖት
ሞረሽ ብለን በአንድነት  ለአገር ክብር  ነፃነት
ፋኖ ብለን ሁላችን  ለሰንደቅ ዓላማ መለዮ እምነት
ሞረሽ ብለን፣ ፋኖ ብለን ለድል  ለእናት አገር ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት

ምንጊዜም ኢትዮጵያ!

ሕዝብ አሸናፊነው!

ማዝያ 24/2004